# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 73 መስከረም 28 2002 ዓ.ም ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ወያኔ ይህን ምርጫ ተብዬ እያዘጋጀ ያለው ዴሞክራሲያዊ ለመባል ብቻ ሳይሆን በእውነተኛ ምርጫ የደረሰበትን የ97 ውርደት ተቃማዊዎች ምንም ልትንቀሳቀሱ በማትችሉበት ሁኔታ በውሸት ምርጫ አዋርዶ "በዝረራ አሸነፍኩ" ብሎ ለመፎለል ነው::

## ግንቦት 7 በአሜሪካን አገር ውጤታማ ስብሰባ አደረገ። ለትግሉ ማጠናከሪያም በርካታ ገንዘብ ተሰበሰበ

የግንቦት 7 ንቅናቄ የፍትህ፣ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ባለፈው እሁድ በዳላስ ከተማ ባደረገው ስብሰባ በርካታ ሰዎች የተገኙ ሲሆን፣ በስብሰባውም ላይ የግንቦት 7 ሊ/መንበር ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ፣ የቀድሞው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ፕሬዚዳንት ተክለሚካኤል አበበና በየመን የቀድሞው የኢትዮጵያ ዲፕሎማት አቶ ዘነበ ሀ/ማርያም ንግግር አድርገዋል።

ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ እንደተናገሩት በ1997 ምርጫ ወቅት ወያኔ ተቃዋሚዎችን በኢንተር-ሀምወይ ስም ሲከስ እንደነበር አስታውሰው፣ በዘንድሮው ምርጫ ደግሞ በኢንተር-ሀምወይ ምትክ የደርግ ርዝራዦች የሚል ቅጽል ለተቃዋሚዎች ማውጣቱን ገልጸዋል።

"እጅግ የሚገርመው ግን እነግርማ ብሩን የመሰሉ የደርግ ባለስልጣናትን በጉያው ታቅፎ፣ የህወሀት ባለስልጣናት የነበሩትንና አሁን በተቃዋሚወች ጎራ የተሰለፉትን እነ ስየ አብርሀንና ገብሩ አስራትን ጭምር የደርግ ቡችሎች" ብሎ መጥራቱ ነው ያሉት ዶ/ር ብርሀኑ የወያኔ አገዛዝ በደርግ ጊዜ ከነበረው አገዛዝ ያልተሻለ፣ እንዲያውም በአንዳንድ ነገሮቹ የሚብስ መሆኑን ለግንዛቤ የሚረዳ ማነጻጸሪያ በማቅረብ አብራርተዋል።

"በፍትህ ስርአቱ በኩል ደርግ ለፖለቲካ አላማው ማስፈጸሚያ ፍርድ ቤቶችን ማዋረድ አንዳላስፈለገው፣ ይህም ዜጎች በፍትህ ሥርዓቱ ላይ የነበራቸውን እምነትና ተስፋ ጠብቆ እንዲኖሩ ያስቻለ መሆኑን ጠቅሰው ወያኔ/ኢህአደግ ግን በአለም አቀፍ ለጋሾች ፊት ወዳጅነት ለማትረፍ በነበረው ምኞት አኩይ አላማውን በፍርድ ቤት ስም ለማስፈጸም በተከተለው ስልት ለዘመናት የቆየውን በፍትህ ላይ የመተማመን ባህል የናደ ብቻ ሳይሆን ከተወገደም በኋላ ቢሆን ከችግሩ ለማገገም ብዙ ጊዜ የሚወስድብን በሽታ ጥሎ አንደሚያልፍ ተናግረዋል። የአገር መከላከያን አስመልክቶ ወያኔ የዘረጋው መዋቅር ለአገሩና ለዳር ድንበሩ ደንታ የሌለው በቋንቋና በዘር ተከፋፍሎ እርስ በእርስ በጥርጣሬ በጎሪጥ የሚተያይ በዚህም ምክንያት በጋራ ጉዳይ ላይ በአንድነት ለመቆም ይችላል ተብሎ እምነት ለማሳደር የማይቻል ሠራዊት በመፍጥር በደርግ ጊዜ ያልነበረ ነገር ግን የከፋ ሁኔታን ፈጥሮአል ብሎአል።

ሊ/መንበሩ አያይዘውም ወያኔ ከምርጫ 97 በኋላ ሙሉ በሙሉ የሚተማመንበትን መከላከያ ለመፍጠር ሲል የአዛዥነቱን ቦታዎች ሙሉ በሙሉ በአንድ ብሄር ስር ማዋሉን፣ አሁን ያለው ሰራዊት የአገራችን ድንበር ተቆርሶ ለሌላ አገር ሊሰጥ ነው ብለው ተቃውሞ የሚያነሱ ዜጎችን ለመምታት የተዘጋጀ አስገራሚ የመከላከያ ሀይል እንዲሆን ማድረጉን ገልጸዋል። **ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## ወያኔ በኦሮሞ ተወላጆች ላይ የሚያደርገውን ጥቃት ቀጥሎበታል

አሜሉ ሁንዴሳ እና ድርቢ ገዳ የተባሉ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸውን ወጣት የኦሮምኛ ድምጻዊያን አስሮ የከፋ ሰቆቃ እየፈጸመባቸው እንደሆነ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ዜና የአዲስ አበባ ወኪሉ ጠቅሶ ዘግቧል። ካለፈው ወር አንስቶ እስከ አሁን በእስር ላይ የሚገኙት ድምጻውያን በተለምዶ ማእከላዊ እየተባለ በሚጠራው የፌዴራል ወንጀል ምርመራ ከፍተኛ ሰቆቃ እየተፈጸመባቸው እንደሆነ ታውቋል። ወጣት ድምጻውያኑ ለእስራትና ለሰቆቃ የተዳረጉት የኦሮሞ ተፋላሚዎችን በዘፈኖቻችሁ ታወድሳላችሁ ተብለው እንደሆነ ተጠቅሷል። በወያኔ ከፍተኛ ሰቆቃ የሚፈጸምባት እንስቷ ድምጻዊት ድርቢ ገዳ በቅርቡ ምስራቅ ሸዋ ውስጥ የተቋቋመው "የኦሮሞ ጀግኖች የሙዚቃ ቡድን" አባል መሆኗ ተገልጿል።

በተመሳሳይ ከአስራ አምስት ቀን በፊት በኦነግ ዜና መታሰሩ የተነገረለት ታዬ ደንዳ የተባለ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ በማእከላዊ ከአስራ አምስት ቀን በላይ ከፍተኛ ሰቆቃ ከተፈጸመበት በኋላ አሁን የት እንዳለ እንደማይታወቅ ተገልጿል። ተማሪ ታዬ ደንዳ በህይወት ይኑር ወይም ደግሞ ይሙት የታወቀ ነገር እንደሌለ የገለጸው የኦነግ ዜና ባለፉት ሳምንታት ከአዲስ አበባ እና ከኦሮምያ በርካታ ኦሮሞዎች መታሰራቸውን መዘገቡን አስታውሷል። **ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

ግዜ

## በሱዳን መንግስትና በወያኔ መካከል የሚደረገውን የድንበር ማካለል በተመለከተ የወያኔ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያወጣው ሪፖርት ህዝብን ማደናገሪያና ጊዜ መግዣ ነው ተባለ

ሁለት የኢትዮ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ አባልና አንድ አካባቢውን በደምብ የሚያውቁ ኢትዮጵያውያን ለግንቦት ሰባት ድምጽ በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ እንደገለጹት፣ የሱዳን መንግስት ቦታውን አስቀድሞ ተረክቦ የሱዳን ገበሬዎች አካባቢውን በማረስ ላይ መሆናቸው እየታወቀ፣ የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሬት የማካለል ደረጃ ላይ አልደረስንም ማለቱ ፍጹም ሀሰት ነው ብለዋል።

አቶ ሊቁ እጅጉ ፣ አቶ አንዳርጌ መራና አቶ አዳነ አጣናው እንዳረጋገጡት በጎንደር አካባቢ የሚገኙ ገበሬዎች አምና የዘንድሮው ሰብላችሁ የመጨረሻ ነው ተብሎ እንደተነገራቸው፣ በተወሰኑት አካባቢዎች ደግሞ ገበሬዎች ሙሉ በሙሉ ተነስተው የሱዳን ሰራዊት አባላት መረከባቸውን ገልጸዋል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## በአማራው ክልል አቦላ ተብሎ በሚጠራ የገጠር ቀበሌ የሚኖሩ ገበሬዎች በወያኔ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ የፖሊሶችን መሳሪያ በመቀማትና በመደብደብ ገጥጹ

ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ አንድ አርሶ-አደር ለግንቦት 7 የአገር ውስጥ ዜና ዘጋቢ እንደገለጹት፣ በባህር-ዳር ዙሪያ ወረዳ የሚገኙ አርሶ-አደሮች መሬታቸውን ለአበባ እርሻ ልማት እንዲያስረክቡ ከወየኔ ባለስልጣናት በመታዘዛቸው እርምጃውን ለመውሰድ ተገደዋል።

አርሶ አደሩ እንደገለጹት በርካታ ቤተሰብ የሚተዳደርበትን ለም ቦታ ለውጭ አገር አበባ አምራቾች ለማስረከብ በአካባቢው የተገኙት ፖሊሶች፣ ከህዝቡ በተነሳባቸው ተቃውሞ ብዙዎቹ ሸሽተው ሲያመልጡ ሁለቱ ግን መሳሪያቸውን ተቀምተውና ተደብድበው ተለቀዋል። በሁኔታው የተደናገጡት የአካባቢው ባለስልጣናት ወዲያውኑ ቅልብ የወያኔን የፌደራል ፖሊስና የመከላከያ ሰራዊት አባላትን ያሰማሩ ሲሆን፣ ገበሬዎቹ ግን በአቋማቸው መጽናታቸውን ለማወቅ ተችሎአል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ኢትዮጵያ ለመኖሪያነት ከሚመረጡት የዓለም አገሮች ውስጥ በመጨረሻው ረድፍ መገኘቷን የዩ.ኤን.ዲ.ፒ ሪፖርት ገለጸ

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም በእንግሊዝኛው አጠራር ዩ.ኤን.ዲ.ፒ ከትናንት ወዲያ ማክሰኞ መስከረም 26 ቀን 2002 ዓ.ም ባወጣው ሪፖርቱ በአለም ላይ ካሉት ለኑሮ እጅግ ተመራጭ ካልሆኑ አገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ስትሆን፣ በደረጃ ሰንጠረዡም 171ኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧታል።

በሪፖርቱ ኤርትራ ከኢትዮጵያ በእጅጉ ለመኖሪያነት የተሻለች አገር ተብላም ተመርጣለች።

"ወያኔ ሌት ተቀን የህዝቡ ኑሮ ተሻሽሎአል" እያለ እንደ ልቡ በሚፈነጭበት ራዲዮና ቴሌቪዥን ህዝብ የማደንቆሩን ስራ ቢገፋበትም፣ የኢትዮጵያ ህዝብ የኑሮ ደረጃ ግን ከእነ አፍጋኒስታን፣ ኮንጎና ሴራሊዎን ተርታ ከመመደብ አለማምለጡን ሪፖርቱ አምልክቷል።

በሪፖርቱ ከቀረበው መረጃ በጣም አስገራሚው ነገር የኤርትራ ደረጃ ሲሆን፣ ወያኔ ነጋ ጠባ "ኤርትራ ኢኮኖሚዋ ደቋል፣ እንደ አገር ልትፈራርስ የቀራት አንድ ሀሙስ ነው ወዘተ" እያለ ቢያናፋም፣ በዩ.ኤን.ዲ.ፒ የቀረበው ሪፖርት እንደሚያመለክተው ግን በንጽጽር ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተሻለች አገር መሆኗንና በደረጃ ሰንጠረዡም ከኢትዮጵያ በስድስት አገሮች ከፍ ብላ በ165ኛ ደረጃ መገኘቷን ገልጿል። የኢትዮጵያ ደረጃ በየአመቱ እያስቆለቆለ መሄዱን ከሪፖርቱ መረዳት የተቻለ ሲሆን ፣ ከዛሬ ሀያ አመታት በፊት በአጠቃላይ የኑሮ ደረጃ ትበልጣቸው የነበሩት አገሮች ኢትዮጵያን ቀድመው ወደ ላይ ሲወጡ፣ አገራችን ግን ቁልቁል መውረዱን ተያይዛዋለች።

ተረት ተረቱን ወደ ዜና ለውጠው ህዝቡን በባዶ አየር የሚነፉት የወያኔ የፕሮፓጋንዳ ማሽኖች ይህን አስደንጋጭ ዜና ከመዘገብ መቆጠባቸውን ለማወቅ ተችሏል።

የዩ.ኤን.ዲ.ፒ ሪፖርት በጥናቱ ውስጥ የገቢን፣ የትምህርትን፣ የጤናንና የመሳሰሉትን ጉዳዮችን በግምት ውስጥ አስገብቶ የሚያጠና ሲሆን፣ በዘንደሮው ውጤት ኖርዌይ፣ አውስትራሊያና አይስ ላንድ ከአንድ እስከ ሶስተኛ ያለውን ደረጃ መያዛቸውንም ገልጿል ።

# የወያኔን ሕገ-ወጥ የመሬት ስጦታ እንቃወማለን፤ የኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅሞችን የሚያስጠበቅ መንግሥት ለመመስረት ታጥቀን ተነስተናል

በአሁኑ ወቅት ውዲቷ አገራችን ኢትዮጵያ መንግሥት አልባ ናት። በዚህም ምክንያት ሚኒሊክ ቤተመንግሥት ውስጥ የመሸገው የወንበዴዎች ቡድን የሚያደርስባት ጥቃት በየእለቱ እየጨመረ፤ አድማሱም እየሰፋ ነው። ጥቃቱን የከፋ የሚያደርገው ይህ ፀረ_ኢትዮጵያ የወንበዴዎች ቡድን "መንግሥት ነኝ" ብሎ መቀመጡና ከሌሎች አገሮችም ጋር በኢትዮጵያ ጉዳይ የሚዋዋል መሆኑ ነው። ይህ ቡድን እስካሁን ከሌሎች አገሮች ጋር ከፈረማቸው ውሎች ለኢትዮጵያ ጥቅም ሲል ያደረገው አንድም አይገኝም። የብድርና የእርዳታ ውሎች የቡድኑ የፋይናንስ ምንጮች በመሆናቸው የሚፈጽማቸው ሲሆን ከዚያ ውጭ ያሉትን በሙሉ ኢትዮጵያን ለመጉዳት አስቦና አቅዶ የፈረማቸው ናቸው።

አሁን ደግሞ ከሱዳን መንግሥት ጋር ለዓመታት ውስጥ ውስጡን ሲያደርገው የነበረው የመሬት ስጦታ የክህደት ውል መጠናቀቁ እየተሰማ ነው:: ይህ ውል ርዝመቱ 1600 ኪሚ፣ ስፋቱ ደግሞ ከ30 እስከ 60 ኪሚ የሚደርስ እጅግ ለም የሆነ መሬትን ለሱዳን ይሸልማል። "ለመሆኑ ከሱዳን ወገን ግፊት እንኳን በሌለበት በአሁኑ ሰዓት የመሬት ስጦታ ለመስጠት ወያኔን ምን አነሳሳው?" ለሚለው ጥያቄ ሁለት ምላሾች አሉት ብለን እናምናለን።

1. ወያኔ ፀረ_ኢትዮጵያ የሆነ ቡድን ነው። ከዚህ በፊት የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅሞችን የሚጎዱ በርካታ ተግባራትን ፈጽሟል። አንዳንዶቹ የወያኔ ተግባራት ለሚቀጥሉ ብዙ ትውልዶች የሚተርፉ ጎጂ ውጤቶችን አስከትለዋል። የቅርብ ጊዜ የወያኔ የክህደት ተግባራትን እንኳን ብናነሳ የባድሜ ጦርነት፣ የአልጀርሱ ስምምነት፣ የሄጉ የፍርድ ውሳኔ አፈፃፀም፣ የሶማሊያው ጣልቃ ገብነት እና በአባይ ወንዝና ተፋሰሶቹ አጠቃቀም ላይ እየተረቀቁ ያሉት ውሎችን ማስታወስ ይበቃናል። ሰፊ ለም መሬታችንን ለሱዳን የማስረከብ ተግባር ከወያኔ ተከታታይ ፀረ_ኢትዮጵያ ተግባራት አንዱ ነው። ለሱዳን ለም መሬታችንን መስጠት ዘርፈ ብዙ ጉዳት ስላለው የወያኔ የእርካታ ምንጭ ነው። ወያኔ እድል ከተሰጠው ኢትዮጵያን የሚጎዳ ማናቸውም ተግባራት ከመከወን የማይመለስ እኩይ ቡድን ነው።
2. ኢትዮጵያዊያን ወያኔ በጉልበት የያዘውን ሥልጣን በጉልበትም ቢሆን በመንጠቅ የአገራቸውና የነፃነታቸው ባለቤት ለመሆን መቁረጣቸው ወያኔን አስደንግጦታል። እናም የነፃነት ታጋዮች ይጠቀሙበት ይሆናል ብሎ ያሰባቸውን መንገዶች ለመዝጋት የማይከፍለው ዋጋ የለም። "ይህን ያህል መሬት ልስጥህና የተረፈችዋን ከራሴ አገር ዜጎች ተከላከልልኝ" ማለት ከጤነኛ ሰው አዕምሮ የማይጠበቅ ቢሆንም ለወያኔ መሪዎች በሽተኛ ጭንቅላት ግን ትልቅ ግኝት ነው:: ወያኔ ለሥልጣኑ ሲል እስከ ምን ድረስ ሊሄድ እንደሚችል ከዚህ በላይ ምን አመላካች ይኖራል?

የመለስ ዜናዊ የግል መዝናኛ የሆኑት ራሳቸውን "የተከበሩ ..." እያሉ የሚጠሩ የፓርላማው አሻንጉሊቶች ስለዚህ ድንበር ስጦታ ገና አልሰሙ ይሆናል። ጥቂቶች ሰምተው ከሆነም የመረጃቸ ምንጫቸው እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግንቦት 7 ድምፅ ራድዮ፣ ሱዳን ትሪቡን ጋዜጣ፣ የአሜሪካ ወይም የጀርመን ድምፅ ራድዮዎች መሆናቸው ጥርጥር የለውም። እያጨበጨቡ ያፈረጠሙት ሥርዓት ለቅሶን ዘፈን፤ ንዴትን እርካታ፤ ሰቆቃን ፍስሃ አድርጎ ነው የሚያሰማቸው። የሚያርሱትን ማሳ የተነጠቁ ገበሬዎች እያለቀሱ፤ ዳር አገር እየተወሰደ መሃሉ ዳር ሲሆን እነሱ በጌታቸው የሽሙጥ ቀልዶች ሲፍነከነኩ ማየት ያሳፍራል፤ ያስጠይቃልም::

አሁን ዋናው ጉዳይ "ምን ይደረግ?" ነው። ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለተለያዩ አካላት የሚከተሉትን መልዕክቶች ያስተላልፋል::

### 1. ለኢትዮጵያ ሕዝብ

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! የቋራው አንበሳ የአፄ ቴዎድሮስ ቀየ፤ አፄ ዮሃንስ የተሰውለት ምድር፤ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ድሆች አያት ቅድም አያቶታችን በደምና በአጥንታቸው ያፀኑት ድንበር ዛሬ በስጦታ እየተሰጠ ነው። ይህን በዝምታ መመልከት በትውልድም በታሪክም ያስጠይቃል:: በአገር ውስጥም በውጭ አገራት የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን የሚያስተባብረን የአገራችን ሉዓላዊነት ነው፤ በጋራ እንነሳ። ሱዳን ገፀ_በረከት ነው የቀረበላት፤ እኛ የምንፋለመው ገፀ_በረከት አቅራቢውን ወያኔን ነው። ወያኔን በአስቸኳይ ማስወገድ የመፍትሄዎች እምብርት ነው።

### 2. ለፓለቲካና ሲቪል ማኅበራት

በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ልዩነቶች ቢኖሩንም በአገር ጉዳይ ግን የጋራ አቋም ልንይዝ ይገባል። አባቶታችንና እናቶቻችን የውጭ ጠላትን ለመመከት የውስጥ ቅራኔን ወደ ጎን አድርጎ በጋራ መነሳትን አውርሰውናል። ወያኔ ከውስጣችን ቢወጣም በባህርዩ ባዕድ ነው። ኢትዮጵያዊያን በባዕድ ወረራ ወቅት የምናሳየው ኅብረት ዛሬ በወያኔ ላይ እንድገም::

### 3. ለሱዳን ሕዝብ እና መንግሥት

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሱዳን ሕዝብ ከፍተኛ አክብሮት አለው። የሱዳን ሕዝብም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ አክብሮት እንዳለው እናውቃለን። በችግር ወቅት አንዱ ወደ ሌላው እየተሰደደ ወዳጅነታቸውን በከፉ ቀኖች ሳይቀር አስመስክረዋል:: ይህ ለዘመናት የዘለቀው የሁለቱ አገሮች ሕዝቦች ወዳጅነት ዛሬ በወያኔ ተንኮል ሊደፈርስ አይገባም። የወያኔ ስጦታ በማር የተለወሰ መርዝ ነውና ስጦታውን መቃወሞ አርቆ አስተዋይነት እንደሆነ እንድትረዱልን እንጠይቃለን።

የሱዳን መንግሥትም በረዥም ጊዜ ሁለቱንም አገሮች የሚጎዳ በመሆኑ ለአገራቱ ዘላቂ ጥቅም ሲባል አሁን ከወያኔ ጋር የሚያደርገው ድርድር እንዲያቆም እንጠይቃለን።

### 4. ለዓለም ዓቀፍ ማኅበረሰብ

ወያኔ ከሱዳን መንግሥት ጋር እያደረገው ያለው ውል የኢትዮጵያ ሕዝብ አጥብቆ የሚቃወመው በመሆኑ ለአካባቢው ሰላም ተጨማሪ ፈተና ከመፍጠሩ በፊት የዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ እልባት እንዲሻለት አበክረን እናስገነዝባለን::

የወያኔን ሕገ_ወጥ የመሬት ስጦታ እንቃወማለን፤ የኢትዮጵያ ዘላቂጥቅሞችን የሚያስጠበቅ መንግሥት ለመመስረት ታጥቀን ተነስተናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!**

## ግንቦት 7 በአሜሪካን አገር ... ከገጽ 1 የዞረ

ወያኔ ባህላዊ ተቋማትን ለማዋረድ ሳይታክት እንደሚሰራ የተናገሩት ዶ/ር ብርሀኑ በቅርቡ በኢትዮጵአ ኦርቶዶክስ ቤተክርሲያን ውስጥ ወያኔ እየሰራ ያለውን ተንኮል ሲገልጹ ደግሞ "ማህበረሰቡ ትልቅ ክብር በሚሰጣቸውና የማንነቱ መግለጫ የሆኑትን የሀይማኖት ተቋማት እንደ ማንኛውም አልባሌ ነገር ለፖለቲካ ስራ መጠቀሚያ ሲያደርገው ለተመለከተ ይህ የአገር ምሰሶ የሆኑ ተቋማትን የማፈራረስ ሂደት አገሪቱን በጠቅላላ ከመብላቱ በፊት ያቆማል ወይ? ብለን እንድናስብ የሚያስገድደን ነው። በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን ውስጥ የሚካሄደው ትርምስ መስመሩን ጥሶ ጳጳሳት ቤታቸው ውስጥ በቦዘኔ የሚደበደቡበት፣ ትላልቅ የሀይማኖት አባቶች አገር ትተው ወደ ጎረቤት አገር የሚሰደዱበት፣ አንቱ የሚባሉ የሀይማኖት አባቶች በእምነታቸውም ሆነ በቃላቸው መጽናት ፍጹም የተሳናቸው ደረጃ የደረሱበት ፣ ማህበረሰቡ መአት ነው የመጣብን ብሎ እስከሚያምን ድረስ ምንም ሊተማመንበት የሚችለው ተቋም እንዳይኖር እየተደረገ ያለበት አደገኛ ሁኔታ ነው የተፈጠረው" ብለዋል።

ሊ/መንበሩ በመጨረሻም የአገሪቱን ተቋማትም ሆነ አገሪቱን በመላ ከጥፋት ጎዳና መመለስ የሚቻለው ከንፈር በመምጠጥ ሳይሆን በተግባር ነው ካሉ በኋላ ፣ ሁለት የተግባር እርምጃወችንም አስቀምጠዋል። አንደኛው የተግባር እርምጃ ወያኔን በተባበረ ክንድ መጣል ሲሆን፣ ሌላው እርምጃ ደግሞ ወያኔ በአገራችን ላይ እያደረሰ ላለው ጥፋት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከመተባበር መቆጠብ እንደሆነ አስረድተዋል። "ይህን ካደረግን" ይላሉ ዶ/ር ብርሀኑ "ይህን ካደርግን እንወዳታለን የምንላትን አገር ለዘላቂነት ብቻ ሳይሆን ለዘመናት በወረደባት የአምባገነን አገዛዝ ከወደቀችበት የምትነሳበትንና ለሁሉም ልጆቹዋ እኩል የሆነች ነፃ አገር ቢያንስ ልጆቻችን እንዲኖራቸው በስራችን አረጋገጥን ማለት ነው" ብለዋል።

በስብሰባውም ወቅት ለግንቦት 7 ማጠናከሪያ ከተጠበቀው በላይ ገንዘብ እንደተሰበሰበም ለማወቅ ተችሏል።

## ወያኔ በኦሮሞ ተወላጆች ላይ ... ከገጽ 1 የዞረ

ማእከላዊ በተባለው የማሰቃያ ስፍራ ሗላቀሩና ነፈሰበላው የወያኔ ቡድን የበርካታ ዜጎችን ጥፍር በፒንሳ መንቀሉ፤ የወንድ ብልት ላይ ብሎኬትና ጠርሙሶች እያንጠለጠለ የዘረ ፍሬ ማምከኑና አሁንም በዚህ አረመኔያዊና ፋሺስታዊ ጭካኔው መቀጠሉ ይታወቃል። የግንቦት ሰባት ድምጽ ይህን አሰቃቂ ግፍ በዜጎች ላይ የሚፈጽሙ ገራፊዎችን ስም በከፊል መናገሩ አይዘነጋም።

ለብሄር ብሄረሰብ መብት ቆሜያለሁ እያለ ርካሽ ፕሮፓጋንዳ የሚነዛው አረመኔዊ የወያኔ ቡድን አንድን ሰው በዘውጌ ማንነቱ ብቻ እንደሚያጠቃው በዜጎች ስቃይና ጣር በተሞሉት አስራ ስምንት አመት የግፍ ዘመኑ በተደጋጋሚ የታየ መሆኑ ይታወቃል።

በወያኔ ዘመን ኦሮሞ ሆኖ መፈጠር ብቻ ለከፍተኛ ስቃይና መከራ እንደሚያበቃ በበርካታ ኦሮሞዎች ላይ ከሚደረሰው ሰቆቃ በግልጽ የሚታይ ሲሆን፡ በግፉ መብዛትም የተነሳ የቃሊት እስር ቤት ብሄራዊ ቋንቋ ኦሮምኛ እንደሚባል ይታወቃል። ወያኔ ኦሮሞውን ጠባብ አማራውን ነፍጠኛና ለሌሎቹም ዘውጌዎች የተለያዩ ቅጽሎች እየሰጠ ህዝቡን ተራ በተራ እየፈጀ እንደሆነ ማንም አይስተውም።

ወያኔ እስካሁን ድረስ ብሄር ከብሄር እየለየ፤ አንዱን በአንደኛው ላይ ለማስነሳት እየሞከረ በከፋፍለህ ግዛው የፋሺስት መርህ የኢትዮድያን ህዝብ ረግጦ የሚገዛው በእርሱ ጥንካሬ ሳይሆን በተቋዋሚዎቹ ድክመት መሆኑን የገለጹት አንድ ታዛቢ የፓለቲካ ድርጅቶች በወገን ላይ የሚደረሰውን ፋታ የሚነሳ ሰቆቃና አደጋ ላይ የወደቀውን የሀገሪቱን ህልውና ከግምት ውስጥ አስገብተው ነገ ዛሬ ሳይሉ ግንባር ፈጥረው የሚፈጸመውን ግፍና ሰቆቃ ማስቆም አለባቸው ብለዋል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## ማብራሪያ ምርጫ 2002 በተመለከተ የግንቦት 7 አቋም ማብራርያ ክፍል 3 የመጨረሻ ክፍል

በመጨረሻም ሕዝብ በምርጫ ለውጥ ይቻላል የሚለውን እምነት ጨርሶ ከአዕምሮው አውጥቶ በምትኩ የሕዝቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ከወያኔ በጎ ፈቃድ ጋር እንደተያያዘ ቆጥሮ በፍርሃት እንዲወጥ የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካና የስነልቦና ጦርነት ያለማቋረጥ ተደርጎበታል፡፡

ለማስረጀም ያህል

- የምርጫ 97 ዋና ዋና ተሳታፊ የነበሩ ወጣቶችን፤ ነጋዴዎችና የገጠር ነዋሪዎችን በእሥር፤ በስደትና በሞት ሲቀጣ ሌሎችን ደግሞ እየተጠሩ በማስፈራራት፤ በመተዳደሪያ ሥራቸውና ንግዳቸው ላይ እገዳ በማድረግ፤ ሥራን በማሳጣት፤ ያለአግባብ ግብር በመጫን ... ሁለተኛ ከተቃዋሚ ጎን እንዳይቆሙ ያስፈራራል።
- ትምህርቱን ጨርሶ ወደ ሥራ ፍለጋ የሚሰማራውን ተመራቂ ወጣት ሥራ ለማግኘት ወያኔን መደገፍና የወያኔ ተለጣፊ ድርጅቶች ውስጥ አባል መሆን ግዴታ እያደረገበት ነው።
- በማንኛወም መንገድ ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ግንኙነት የሚፈጥር ሰው በራሱና በቤተሰቦቹ ኑሮና ደህንነት ላይ አደጋ እንደሚፈጠር ቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ይነገረዋል።

ከላይ በተዘረዘሩት እርምጃዎች አማካይነት በምርጫ 2002 አሸናፊ አድርጎ የሚያወጣውን «ተቃዋሚዎችን የማዳከም፤ የሲቪል ማኅበራትን የፖለቲካ ተሳትፎ ማጥበብንና የሕዝብንም ቅስም የመስበር የምዕራፍ አንድ ዝግጅቴን አጠናቅቂያለሁ» ብሎ አምኗል። የሁለተኛው ምዕራፍ መርሃ ግብሩን ደግሞ በቅርቡ እንደሚጀምር አንዳንድ ሁኔታዎች እያመለከቱ ነው። በዚህ በሁለተኛ ምእራፍ የሚጠበቀው ዋነኛ እርምጃም ወያኔ ለራሱ በተመቻቸ የጊዜ መስኮት ውስጥ ለምርጫ ውድድር ዝግጁ ነኝ ብሎ ማወጅና ለምርጫውም አጃቢዎችን መፈለግ ነው። ለዚህም የሚጠቀምበት ዘዴዎች የሚከተሉትን እንደሚመስሉ ይጠበቃል፤

- በአለቀ ሰዓት ለሚሳተፉ ተቃዋሚዎች የተወሰነች የሚዲያ ዕድል መስጠት፡ ይህም እድል እንደ ምርጫ 97ቱ ለፓርቲዎች የሚሰጥ ሳይሆን ለግለሰብ ተወዳዳሪዎች እንዲሆን ማድረግ፤ በዚህም ከ500 በላይ የፌደራል ፓርላማ ተወዳዳሪና በሺዎች የሚቆጠር የክልል ተወዳዳሪ በሚሰጠው 5 ደቂቃ ምንም ሳይናገር ጊዜውን እንዲጨርስ ማድረግ፤
- ከተወሰነላቸው ወንበር በላይ ለማሸነፍ ዕድሉም ሆነ የመጋፈጥ ፍላጎት ላላቸውም ለሌላቸውም ኃይሎች በመንግሥት ስም የገንዘብ ድጎማ ማድረግ፤
- ይህንን ውድድር አልባ የሆነ ምርጫም ለውጪ ዓለምና ለእርዳታ ሰጭ አገሮች እንደ ዲሞክራያዊ ተግባር ለማሳዬት ይረዳ ዘንድ የውጭ ታዛቢዎችን መጋበዝ፤
- ብዙ የተማረ የሰው ሃይልና ምናልባትም በሌላው ክልል አመለካከት ላይ "ተጽእኖ" ሊያመጡ ይችላሉ ተብለው የሚታመኑ ዋና ዋና ከተሞችን፤ በተለይም አዲስ አበባን ከሌላው ክልል ምርጫ ለይቶ ምንም ለውጥ በማያመጣ ጊዜ ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግ፤
- በመጨረሻም እየተሰማ ያለው በዚህ በወያኔ ተውኔት ለመሳተፍም ተቃዋሚዎች የሥነ ምግባር ስምምነት ከወያኔ ጋር እንዲፈራረሙ ማድረግ ነው።

የ2002 ምርጫን በሚመለከት ወያኔ በሁለት ምዕራፎች ከፍሎ ያደረገው ዝግጅት ከላይ የዘረዘርናችውን ይመስላል። በሕዝብ ወገን ያሉ ተቃዋሚ ኃይሎች የዚህ የወያኔ ተንኮልና አፈና የመጀመሪያ ተጋፋጮች እንደመሆናቸው መጠን ይህንን ያጡታል የሚል ግምት የለንም። ከሕዝቡ አካባቢ የሚሰማው ስሜት ተቃዋሚዎች ምርጫ ውስጥ እንዲገቡ የማይፈልግ መሆኑን በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሕዝብ ለነኘሁ ተቃዋሚዎች እያሰማ መሆኑን ተቃዎሚዎች ከሕዝብ ጋር በሚያደርጉዋቸው ምክክሮች እያስታወቁ ነው፡፡ ግንቦት 7 ንቅናቄ፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች እራሳቸው ካሉበት ዓይነተኛ ይዞታ በመነሳት ምርጫውን አስመልክቶ አስፈላጊውን ምላሽ እንደሚሰጡ ያምናል። ሆኖም ግን የዲሞክራሲና የአገር ማዳን ትግሉ አንድና በጋራም የሚመለከተን ጉዳይ ነውና እኛም ካለንበት ሁኔታ የሚታየንን ለአገር አቀፍ ትግላችን መደረግና መወሰድ ያለበትን አቋም የመግለጽ ግዴታ አለብን ብለን እናምናለን። በዚህም መንፈስ ግንቦት7 ምርጫ 2002ን አስመልክቶ የሚከተሉትን የትግል ጥሪዎች ያደርጋል።

## 4. የግንቦት 7 ጥሪዎች

### 4.1 ጥሪ ኢትዮጵያ ህዝብ

ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመለስና የጥቂት ተባባሪዎችን መሠሪነት በምርጫም ሆነ በሌላ ሁኔታ መንገር "ቀባሪውን እንደ ማርዳት" ይቆጠራል። ሕዝባችን የሚፈልገው ከዚህ አፋኝና አገር አጥፊ የገዢ ቡድን እንዴት መላቀቅ እንደሚችል በተግባር ታግሎ የሚያታግለው ኃይል ነው። በዚህም መሠረት ግንቦት7 የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ 2002ን አስመልክቶ የሚያስተላልፈው መልዕክት የመለስ ቡድን በሰፊ የገንዘብ ወጭ፤ በማያቋርጥ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻና በመጠን የለሽ የሰው ኃይል ማሠማራት ለሚፈጥረው የማደናገሪያ ቲያትር ጆሮውን እንዳይሰጥ ነው።

ደግመን ደጋግመን ለሕዝባችን የምንለው ነፃ ምርጫ ምን እንደሚመስልና ምን ዓይነት ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ሙሉ በሙሉ ነጻ ባልነበረው በ97 ምርጫ አሳይተሃል። በተጨማሪም የወያኔ ምርጫ የራሱ የገዢው ፓርቲ ጨዋታ እንደሆነ በአለፈው የክልል ምርጫ በልዩ ልዩ መልኩ (ለምሳሌ ካርድን ከመቅደድ ጀምሮ እስከ ካርዱ ላይ ተቃውሞ እስከ መጻፍ ድረስ እንዳደረኸው) ለዓለም ሕዝብና ለራሱም ለወያኔ በማያሻማ መልኩ አሳይተሃል። ስለዚህም መጪውን የመለስን የምርጫ 2002 ጨዋታ ችላ ብለህ በሁሉ-ዓቀፍ ተሳትፎ ለዲሞክራሲና ለአገር ግንባታ የሽግግር ሥርዓት መምጣት አምርረህ ለመታገል ቆርጠህ ተነስ። ጉልበትህን፤ ንብረትህንና ቅዱስ የሆነውን መስዋዕትነትህን ነፃነት ለፍትህና አንድነት ትግል ሳትቆጥብ አብረኸን እንድትሰለፍ ጥሪ እናደርጋለን፡፡

### 4.2 ጥሪ ለሃቀኛ ተቃዋሚዎች

የመለስ-በረከት ቡድን በየደረጃው የተበተበውን የአፈናና የማደናገሪያ እርምጃ ገፈት ከእናንተ የበለጠ የቀመሰው የለም። በሕዝብ የተከበሩ መሪዎቻችሁ መታሠር ጀምሮ እስከ አባላቶቻችሁ በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች መዋከብና መታፈን ምን እንደሚመስል ለእናንተ አይነገርም። እንድምታውቁት ከዚህ ሁሉ የእብሪትና የብልግና ድርጊቱ በኋላ ነውር የለሹ የወያኔ ቡድን ከእናንተ ትልቅ ችሮታ ለመጠይቅ ይመጣል። ይህም ችሮታ አሸናፊነቱን አስቀድሞ ባረጋገጠበት ሰአት የምርጫ 2002 አጃቢዎቹ እንድትሆኑ የተለመዱ አማላጆቹንና የማታለያ ቡርቲውን ይዞ ይቀርባል። በዚህም መለስ ከሠለጠነው ዓለም መድረክ ላይ በወጣ ቁጥር በግልፅም ሆነ በውስጠ ታዋቂ ቋንቋ የሚቀርብለትን የምርጫ 97 ዘራፊነቱን ክስ በእናንተ አጃቢነት ሊሰርዝ ይፈልጋል።

እናንተ እኮ የነፃ ምርጫ ቅድመ ሁኔታዎችን የምታውቁ ብቻ ሳትሆኑ የእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ደራሲዎች ናችሁ። እናንተ እኮ የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን አገዛዝ በተመለከተ "ብልጥ ልጅ የሰጡትን ይዞ ያለቅሳል" ከሚል የፖለቲካ ቀልድ እንዳለፈ የዓይን ምስክር ናችሁ። ብዙዎቻችሁ እኮ በምርጫ 97 ሕዝባችን ከድል አፋፍ በአጋዚ ጦር እየተደበደበ ወደ ታች እንዲወርድ ሲደረግ አብራችሁ ገፈቱን የቀመሳችሁ ናችሁ። ወያኔ ይህን ምርጫ ተብዬ እያዘጋጀ ያለው ዴሞክራሲያዊ ለመባል ብቻ ሳይሆን በእውነተኛ ምርጫ የደረሰበትን የ97 ውርደት እናንተን ምንም ልትንቀሳቀሱ በማትችሉበት ሁኔታ በውሸት ምርጫ አዋርዶ "በዝረራ አሸነፍኩ" ብሎ ለመፎለል ነው፡፡ እነሱ እንደሆን ለራሳቸው ምንም ክብር የላቸውም፡፡ ሕዝብ የሚያከብራቸውን ወገኖች እንደነሱ ሲዋረዱ ማየት ትልቅ ደስታ የሚሰጣቸው ህመምተኞች መሆናቸውን አትርሱ፡፡ ስለዚህ በእኛ እምነት አሁን የሚያስፈልገው ለሕዝባችን፤ ለዓለሙ ማኅበረሰብና ለራሱም ለወያኔ የመለስ-በረከት ቡድን፤ እነሱ የይስሙላ ምርጫ ሲሉና ሕዝቡና የሕዝብ ወገን የሆኑ ሁሉ ነፃ ምርጫ ሲሉ ያለውን ከፀሐይና ከጨለማ ያልተናነሰ ልዩነት በድፍረት ማሳየት ነው። በዚህም እርምጃ እውነተኛ የሕዝብ ወገኖች፣ ሳይጀመር ከወዲሁ በተጨናገፈ ምርጫ ገብቶ ከመተራመስ ይልቅ፣ ለማይቀረው፣ ምርጫን ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ለማድርግ መደረግ ላለበት ትግል አቅማቸውን አስተባብረው ሕዝብን ማደራጀትና ማስተማር የበለጠ ጥቅም እንዳለው አውቀው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል።

### 4.3 ለሚመለከታቸው የዓለም አቀፍ ኃይሎች ማሳወቅ ያለብን አቋም

በአገራችንና በአካባቢያችን የሚሆነው ሁሉ «የብሄራዊ ጥቅማችንን፣ ደህንነታችንንና ሌሎችንም ፍላጎቶቻችንን ይነካል» የሚሉ ዲሞክራቲክ ሀገሮች በኢትዮጵያ ያለው የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ ሥርዓት የመለስ አፈ ጮሌነትና ተራቀቅኩ ባይነት የአንድ ሰው ተውኔት እንደሆነ ከተረዱ ሰንብተዋል። ከሰውዬው ተውኔት በታች ያለው መንግሥት የጥቂት አምባገነኖች አገዛዝ እና በሙስና ከላይ እስከታች የተዘፈቀ መሆኑን ያውቃሉ፡፡ ሆኖም ግን የአገሪቱን የወታደራዊ፣ የፀጥታና የኢኮኖሚ ዋና ዋና ክፍሎች በዘር ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው በሌሎች የዓለም ክፍሎች እንደታየው አደገኛ የርስ በርስ ግጭቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ ብለው ስለሚፈሩ ይጠነቀቃሉ። መለስና ቡድኑን፣ የጄኖሳይድ ዎችና የሌሎችም የሰብዓዊ መብት ተሟጓቾች በከፍተኛ ከሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች በየጊዜው የሚከሷቸው ሰዎች መሆናቸውን እነዚህ መንግሥታት ይህንን ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡

ሆኖም ግን እነዚህ መንግሥታት በዲሞክራሲያዊ ዓላማ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ቢቆሙ እንኳን ሕዝብን ወይም የሕዝብ መሪዎችን ተክተው ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲና ደህንነት ይታገላሉ፤ ወይም ይህንን ሥርአት ያመጣሉ ማለት አይደለም። እንዳያውም የእለት-ተእለት የሀገራቸው ጥቅም ብዙ ጊዜ የቆሙለትን የዴሞክራሲ እምነት በሚጻረር መልኩ ከእንደ እነመለስና-በረከት ቡድን ዓይነቶች ጋር ሲያቆማቸው ደጋግመን አይተናል። ይህ ሁኔታ ምርጫ 2002ን አስመልክቶ አንዳንድ ግንዛቤን እንድንወስድ ያስገድደናል። የውጭ ኃይሎች ምርጫ 2002ን በሚመለከት እንደ ተለመደው "በአንተም ተው አንተም ተው" አቀራረብ ተቃዋሚዎች ከወያኔ ጋር እንድንሰለፍ ይጠይቃሉ። "ደግን ልጅ እናቱ አትወደውም" እንደሚባለውም "እሺ እሺ" የምንላቸውን ክፍሎች አጥብቀው ይጫናሉ።

አሁንም እንደተለመደው በሥልጣኑ የመጣን ሁሉ ወይ ፍንክች የሚለው ወያኔ እነዚህን የውጭ ኃይሎች «እኔ በሚጠቅመኝ መንገድ ባዘጋጀሁት ምርጫ ተቃዋሚዎችን ካላመጣችሁ ብሎ እሪ» ማለቱ አይቀርም። ከዚህም አልፈው እነዚህ ኃይሎች ምርጫ በነፃነት እንዲካሄድ አጥብቀው እንገፋለን ካሉ የመልስ-በረከት ቡድን ከተወዳዳሪ ሌሎች አገሮች (ለምሳሌ ቻይና) ጋር የጠበቀ መቀራረብን እንደሚያደርግ ግልጽ ምልክቶችን እያሳዬ ነው። እንደሚታወቀው ይህንን ስናይ የመጀመሪያ ጊዜያችንም አይደለም። እነዚህ የምእራብ መንግስታት ይህም ወያኔ አካሄድ ያሰጋቸዋል፡፡

በሃገራችን ዕውነተኛ መፍትሄ ላይ በሚችሉትና በሚፈቅዱት ልክ እንዲያተኩሩም እናደርጋቸዋልን።

**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ሃይለ ሀሳብ

## ምርጫ 2002 በተመለከተ የግንቦት 7 አቋም ማብራሪ

. . . ከገጽ 3 የዞረ

እኛ ማድረግ ያለብን፣ እኛ ለዲሞክራሲ፣ ለመልካም አስተዳደርና ኃላፊነት ላለው ሥርዓት ተገዢዎች እንደሆንን በአቋምና በተግባር አጥብቀን ማስረዳትና ማሳየት ነው። ለዚህም ዋና መለያችን አሁን ባለው የኢትዮጵያ ሁኔታ ተወዳድረን ለማሸነፍ የሚያስችለን ምንም ገደብ የሌለብት ነፃ የምርጫ ሁኔታ ከመፍጠር በታች ምንም ድርድር ውስጥ እንደማንገባ በግልጽ ማቅረብ ይኖርብናል። እነዚህ የውጭ ሰዎች «ለምርጫው በቀረው አጭር ግዜ ውስጥ ለምታነሷቸው ትላልቅና ግዜ ወሳጅ ጥያቄዎች እንዴት ምሳሽ መስጠት ይቻላል? የዛሬውን ግቡልንና ለሚቀጥለው ምርጫ ነገሮች ይስተካከላሉ፤ ዴሞክራሲ ሂደት ነው» ማለታቸው አይቀርም፡፡ መልሳችን «ይህንንማ ከዛሬ አራት አመት በፊትም ሰምተነዋል፡፡ ሁኔታዎች ሲብሱ እንጂ ሲሻሻሉ አላየንም፡፡ ዴሞክራሲ አዝጋሚ ሂደት የሚሆነው አብዛኛው ሕዝብና የፖለቲካ ልሂቁ ትርጉሙ ሳይገባው ሲቀር ነው፡፡ በአገራችን የዲሞክራሲ ትርጉም ፈጽሞ ያልገባቸውና ጣፋጭነቱ የሚመራቸው ዘረኛ በሆነ መንገድ ከገነቡት ሥልጣንና ጥቅም ይነቅናል የሚሉ ጥቂት ኋላቀር ዘረኞች ናቸው፡፡ ለጥቂት ዘረኞች ተብሎ ደግሞ የ80 ሚሊዮን ህዝብ የዴሞክራሱ ፍላጎት ሊገታ አይገባም» የሚል ሊሆን ይገባዋል፡፡ ግዜው አጭር ነው ለሚሉትም መልሳችን «ምርጫው ለሌላ ግዜ ይተላለፍ፡፡ በገዥው ፓርቲና በሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች መሃል እንዴት ምርጫውን ነጻና ፍትሃዊ ማድረግ እንደሚቻል በጋራ ጉባኤ ተቀምጠን መክረን ውሳኔ እስከምንሰጥ ምርጫው ይዘግይ» እንበላቸው፡፡

እኛ ለቆምንለት ሕዝባዊ ዓላማም ከሕዝባችን ጎን ቁመን በመሰለንና የተፈጥሮ መብታችንን ተጠቅመን በቆራጥነት እንደምንታገል ማሳዬት ይኖርብናል። ከዚህ በተረፈ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዘላቂና እውነተኛ ወዳጅነት ከፈለጉ የአገሪቱን የፖለቲካ ችግር ሙሉ በሙሉ አፍኖ የያዘውን መንግሥት ሁኔታውን እንዲለውጥ የሚችሉትን ሁሉ እንዲያድርጉ መጠየቅና ከኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት፡ የአንድነትና የዲሞክራሲ ትግል ፊት በአደናቃፊንት እንዳይቆሙ አጥብቀን ማስረዳትና በማያወላውል መልኩ ማሳወቅ ይኖርብናል። በዚህ ጠንካራ አቋማችን ለጊዜው የምእራቡ አለም መልዕክተኞች ቢጮህም፤ ምናልባትም እነሱም ጊዜያዊ ፍላጎታቸውን ስላላሟላን ሊጋፉን ቢሞክሩም፣ ውለው አድረው የሚያከብሩንን ይሆናሉ፡፡

ለማጠቃላልም ሁላችንም በሚቀጥለው ዓመት በመለስ-በረከት የተደገስችልልን የማደናበርያ የመለስ-በረከት ምርጫ ዓላማዋ ምን እንደሆነ የተረዳን ይመስለናል፡፡ ለባርነት ቀንበር ህጋዊዊ ልባስ መስጠት ብቻ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ለዚህ «ኑና ላሞኛችሁ» የምርጫ ጥሪ መልሳችን የማያሻማ «አንዴ የተሞኘነው ይበቃል» ሊሆን ይገባዋል፡፡ መለስና-በረከት ለምርጫ ድግሳቸው ሲንደፋደፉ እኛ በእነሱ የድግስ ከበሮ ሳንደናገር ሁላችንም አቅማችን በሚፈቅድልን መጠን በሃገራችን ዴሞክራሲ እውን እንዲሆን ወደ ጀመርነው የምር ትግል ፊታችንን በጋራ እንድናዞር የግንቦት7 ንቅናቄ ይጠይቃል። የሃገራችን ሰው "ዱባና ቅል አበቃቀሉ እየቅል" እንዳለው ሁሉ እኛም ለወያኔ «የአንተ የማጭበርበሪያ ምርጫና ነጻ ምርጫ እየቅል» በማለት የሕዝብ ልጆች በአንድ ድምፅ እንንገረው!!

## በአማራው ክልል አቦላ ተብሎ በሚጠራ . . . ከገጽ 1 የዞረ

የወያኔ ባለስልጣናትም የህዝቡን ምሬት ከተረዱ በሁዋላ ሰራዊቱ ወደ ኋላ እንዲመለስ ማድረጋቸውን አርሶ-አደሩ ተናግረው፣ ከጥቂት ቀናት በኋላማ የተቃውሞው መሪዎች ናቸው የተባሉትን አርሶ አደሮች በሌሊት ወደ አልታወቀ ስፍራ እንደወሰዱዋቸው ገልጸዋል። አስታባባሪ የተባሉት አርሶ-አደሮች ከታሰሩ በኋላም የወያኔ ባለስልጣናት በድጋሚ ወደ አካባቢው በመሄድ ነዋሪዎቹን ለማሳመን ጥረት ቢያደርጉም፣ ነዋሪዎቹ ግን ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር ለመነጋገር ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ወደ መጡበት መመለሳቸው ታውቋል።

አሁንም ድረስ ፍጥጫው እንዳልበረደ የተናገሩት አርሶ-አደሩ፣ ወያኔ አካባቢውን በጉልበት ለመውሰድ የሚሞክር ከሆነ ህዝቡ ማንኛውንም አይነት መስዋትነት በመክፈል ለመቋቋም መስማማቱን ተናግረዋል።

ወያኔ በኢንቨስትመንት ስም የአገሪቱን ለም መሬቶች ለባለሀብቶች መቸብቸቡን በመቃወም ግንቦት 7 መግለጫ መስጠቱ ይታዋሳል።

## በሱዳን መንግስትና በወያኔ መካከል . . . ከገጽ 1 የዞረ

"ነገሩ ቀደም ብሎ ያለቀ ነገር ነው" የሚሉት ተወላጆቹ፣ አሁን የቀረው ለሱዳን የተሰጠውን ሰፊ መሬት በችካል መለየትና በህግ ማጸደቅ ብቻ ነው ሲሉ የወያኔን ተንኮል አጋልጠዋል።

አስተያየት ሰጪዎቹ አክለውም የወያኔ አገዛዝ በሱዳን በኩል የሚነሳበትን የኢትዮጵያውያንን ተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ ለመግታት በማሰብ የአገራችንን መሬት እንደ ኬክ እየቆራረሰ መስጠቱ፣ በታሪካችን ካጋጠሙን ገዢዎች ሁሉ የተለየ ያደርገዋል ብለዋል።

በአጼ ሚኒሊክ ጊዜ ከሱዳን ጋር የተደረገው ውል የኤርትራን ድንበሮች ጨምር ያካተተ እንደነበር ያስታወሱት አስተያየት ሰጪዎቹ፣ በኤርትራ በኩል ያለው መንግስት አገሩን የሚወድ በመሆኑ ከሱዳን ጋር ምንም የድምበር ድርድር አላደረገም፣ በኢትዮጵያ ያለው ሀይል ግን አላማው አገር ማፈራረስ በመሆኑ ኢትዮጵያን እየቆራረጠ ለጎረቤት አገሮች በመስጠት ላይ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

## በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ኢኮኖሚ መቃወሱን፣ የአገር ውስጥ የጸጥታ ችግር መባባሱን ፤ ረሀብ መስፋፋቱንና ከጎረቤት አገሮች ጋር ያለው ግንኙነት እየተበላሸ መምጣቱን ወያኔ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያስታወቀበት አንድ መረጃ ይፋ አደረገ

የመለስ ዜናዊ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በጥብቅ በሚቆጣጠራቸው የመገናኛ ብዙሀን አማካኝነት የአገሪቱ ኢኮኖሚ እየተመነደገ ነው፣ ሰላሟም እየተጠበቀ ነው እያለ ሌት ተቀን ቢደሰኩርም፣ በአለም አቀፍ ተቋማት ፊት የሚያቀርበው መረጃ የሚያሳየው ግን ተቃራኒውን መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

የወያኔ አገዘዝ የኢትዮጵያን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ በተመለከተ በቅርቡ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ክፍል ተገድዶ ባቀረበው ሪፖርት ላይ ኢትዮጵያ ይህ ነው ተብሎ ሊለካ የማይችል የኢኮኖሚ ቀውስ፣ የእረስ በርስ ግጭትና ረሀብ እንደገጠማት አምኗል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በበኩሉ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታዩት አደገኛ ሁኔታዎች እንደሚያሳስቡት የገለጸ ሲሆን፤ ለግጭቶች መነሻ አንዱ ምክንያት በዘር ላይ የተመሰረተው የፖለቲካ አወቃቀር በመሆኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ፈጥኖ ማስተካከል እንዳለበት አሳስቧል።

የድርጅቱ ሪፖርት አክሎም የወያኔ አገዛዝ የሲቪክ ተቋማትን አሰራር ለመግታት ያወጣውን ህግ መልሶ እንዲቃኘው እንዲሁም በአገሪቱ የሚታዩትን ችግሮች ከተቋማቱም ጋር በጋራ ለማስወገድ መንቀሳቀስ እንደሚገባው አሳስቧል።

ሪፖርቱ፣ በኢትዮጵያ በየጊዜው የሚታየው የብሄር ግጭቶች እንደሚያሳስበው ገልጾ፣ የወያኔ አገዛዝም በአገሪቱ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚታየውን የዘር ግጭት መንስኤ ማፈላለግና መፍትሄ መስጠት ይገባዋል ካለ በሁዋላ፣ በእኤአ 2003 ዓም የመከላከያ ሰራዊቱ በአኙዋኮች ላይ የፈጸመው የሰብአዊ መብት ጥሰት እስካሁን ድረስ አለመመርመሩም እንደሚያሳስበው ገልጿል።

ወያኔ በአገሪቱ ውስጥ ሁሉም ነገር እየተሻሻለ መሆኑን በየጊዜው ሲደሰኩር መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን፣ አሁን ግን ችግሩን በፕሮፓጋንዳ ብቻ መቋቋም ባለመቻሉ ለማመን እየተገደደ ነው።

ግንቦት 7 የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ መሆኑን በተለያየ ጊዜ የገለጸ ሲሆን፣ አገሪቱን አሁን ካለችበት የገደል ጫፍ ላይ መመለስ የሚቻለው ወያኔን በህብረት ታግሎ በማስወገድ ብቻ መሆኑን በማመንም፣ ለዚሁ አላማ መሳካት ሌት ተቀን እየሰራ እንደሚገኝ ይታወቃል።

## የሙት ኑሮ

ኑሮ ካልነው ኖርነው - ካልኖርንም ኑሮ ነው
ቆመን እየበላን፣ ደሞ እየተበላን -ደሞ
እየበላነው፣
እኩል አንባላ፣ እኩል አንናከሥ-ዋጡን
ሰለቀጡን ፍትሕ እያዛቡ፣ የኑሮ ምስጥ ሆኑን።
ካልነው ኖርነው -እንደተባልን ሆነን -
እንዳሉን ተንፍሰን
ፀጥ፣ እረጭ ብለን -ስብዕና ተገፈን፣
ከኛው በዘረፉት -ጉልበት አበጁና
አኖሩን በቡጢ -ገደሉን ባ'ጣና
ተየህ ወዲያ ኑሮ -ደሞ የታለና
ተረምርሞ ኑሮ፣ ኑሮ ተባለና።
እኛ ኩራት ርቆን -እነሱም ፍቅር አጥተው
ኑሮ ካሉት ኖርነው -ነፃነትን አጥተን፣
ነፃነትን ገድለው
ክብር፣ ስብዕና -ትርጉሙ ምንድነው?
የመኖር መለኪያው፣ እስትንፋስ ብቻ ነው?
እንደቀትር ሌባ፣ እንደፈልፈላ ጣይ
ተሣቀን፣ ተሳቅለን -በቤት ባ'ደባባይ
ሲያድኑን እንዳውሬ -ሲልኩብን ሰላይ
ኑሮ ካሉት ኖርነው
በቁም እየሞትነው
እየሞትን አለነው።
ሲስቡን ተስበን፣ ሲገፉን ተገፍተን
በትዕግስት መክተን -ችለነው መቻልን
"ማርም ሲበዛ ይመራል" መቻል አቅል አሳጣን።
ጢብ፣ ጢብ -እንደኳስ
ጣል፣ እቅፍ -ሳም፣ ንክስ
እንደምስማር ካ'ናት - በመዶሻ ድቁሥ ባሩድና
ዕብለት -ለሁላችን ንሥንስ፣ ብረት ተከልለው -
በብረት ከልለው ቋጥረው የሐሰት ክስ
ኑሯችን -ፍርዳቸው -ዘወትር ልክስክስ።
ተሸማቆ ኑሮ-ዘወትር ነጋ ጠባ
ገዥና ተገዥ ሲመዘን ሲለካ
ሙት-ውሎ፣ ሙት-አድሮ-
የኑሮ ገለባ።
በፍርሃት ቆፍንነን -በፍርሃት ታጅለው
እነሥም- አይጠሬ፣ ሁሌ ተሹለክልከው
ዘብጥያ አኑረውን -ከዘብጥያ ኖረው
በዘብ ላይ ጥይት-ከል ደርበው ደርበው።
ኑሮ ካሉት ኖርነው
በቁም እየሞትነው
እየሞትን አለነው።
'እንዳይኖሩ ነዶ፣ እንዳይሄዱ ወልዶ'
መተከዙ ይብቃን -መብከንከን በባዶ
ከውርደት ባሻገር -ከሞት ወዲያ ማዶ
በጥበብ የሚቆም በትግል ተወልዶ፣
ሌላ ዓለም አለ'ኮ -የሚገኝ በሕብረት
የነፃነት ጎራ -የእኩልነት መንደር
ተዛዝኖ መኖሪያ -የሁላችን ኤደን
ይብቃን በቁም መሞት -አሻፈረን እንበል።

**(ሰው ባገሩ :- ጥቅምት 2002 ዓ.ም)**

## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

### የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org